# የኤሌትሪክ ሃይል ሲጠፋ - ሌላ የማገዶና የኤሌትሪክ ማመንጫ በጥንቃቄ ስለመጠቀም

health

Power blackouts - using alternative fuel and electricity generation safely

Amharic

አንዳንዴ ሰዎች መብራት ሃይል ሲጠፋ ለሙቀት፣ ለማቀዝቀዣ፣ ህንጻን ለማድረቅ፣ የቤት መገልገያዎችን ለማሰራ፣ ለማብሰል ወዘተ. ሌላ አማራጭ የሆኑ የማገዶ ወይም የኤሌትሪክ ጀኔሬተር ምንጮችን ይጠቀማሉ።

የካርቦን ሞኖክሳይድ ጋዝ በሚነድ ጭስ ይገኛል ማለት እንደ በትናንሽ የጋዞሊን ሞተሮች፣ ምድጃዎች፣ የሃይል ማመንጫዎች፣ ፋኑሶች፣ በጋዝ የሚሠሩ ወይም ከሰልና እንጨት በማንደድ ይሆናል።

ካርቦን ሞኖክሳይድ የማይታይና የማይሸት ጋዝ ነው። በቤት፣ በጋራጅ ውስጥ ወይም ካራቫን ውስጥ ከተፈጠረ፣ ድንገተኛ ህመም በመፍጠር ህሊናን በመሳትና ሞትን ያስከትላል። ስለ ሰዎችና የቤት እንስሳትም ማሰቡ ጥሩ ነው።

ከቤት ውጭ ለመጠቀም የተሠሩትን የኤሌትሪክ መሳሪያዎች በቤት ውስጥ በምድር ቤት፣ በጋራጅ ወይም ካራቫን ወይም በተከፈተ መስኮት አጠገብ በምንም መንገድ አለመጠቀም። የኤሌትሪክ መሳሪያዎች ማለት እንደ የሃይል ማመንጫ ጀኔሬተሮች፣ የብረት ምድጃ፣ የካምፕ ምድጃ፣ ወይም ሌላ በፔትሮል፣ በLP ጋዝ፣ በመደበኛ ጋዝ ወይም በከሰል የሚቀጣጠል መሳሪያ መጠቀም ያለበት በተለይ አምራጩ በመደበበት ቦታ መሆን አለበት።

## የሃይል ማመንጫ/ጀኔረቶር

አንዳንድ ሰዎች በቤት ውስጥ ያሉትን የኤሌትሪክ መሳሪያዎች ማለት ረፍሪጀራቶርና የማቀዝቀዣ መሳሪያ ለማሠራት ተጨማሪና ተንቀሳቃሽ የሆነ የጀኔረቶር ሃይል ይጠቀማሉ።

ምንም እንኳን በጣም ጠቃሚ ቢሆኑም የሚከሰተውን የቅድሚያ አደጋዎች ለማስወገድ:

- የካርቦን ሞኖክሳይድ መርዝ ከሞተር ማውጣት
- በኤሌትሪክ ንዝረት ወይም በኤሌክትሪክ መግደል እና
- እሳት ይሆናል።

በቤት ውስጥ ነዋሪዎች ጀነራቶሩን ያለችግር ለማሠራት ለማረጋገጥ የሚቀርበውን መመሪያ መከተል አለባቸው።

## ጀነራቶር ስለመግዛት

በቋሚነት የተገጠሙና የማይንቀሳቀሱ ጀነራቶሮች ለቤት ተጨማሪ የሃይል ምንጭ ለማቅረብ በጣም ተስማሚ ናቸው።

ታዲያ ጀነራቶር ከሚያስፈልግ የሃይል መጠን ጋር ተመሳሳይ መሆን ይኖርበታል። ጀነራቶር እንዲሰራ በዚህ ላይ ለመቀጠል ባቀዱት የመብራት፣ የኤሌትሪክ መሳሪያና እቃዎች ላይ ያለውን ምልክት መመልከት ይሆናል።

የርስዎ መሳሪያ ጀነራቶሩ ከሚያቀርበው ብዙ የኤሌትሪክ ሃይል የሚወስድ ከሆነ፣ በዚህን ጊዜ የጀነራቶሩን ፊውስ ሊያጠፋ ወይም የተቀጠለውን መሳሪያ ሊጎዳ ይችላል።

ጀነራቶሩ ለሚፈልጉት ሁሉ በቂ የኤሌትሪክ ሃይል የማያመነጭ ከሆነ፣ ታዲያ ለተለያዩ መሳሪያዎች በፈረቃ እንዲሰሩ የጊዜ እቅድ ማውጣት

## የጀነራቶስ ድህንነት ስለመጠቀም

በቤት ውስጥ ተንቀሳቃሽ የሆነ ጀነራቶር በምንም መልኩ አለመጠቀም። ይህም በጋራጅ፣ ካርፖርት፣ በምድር ቤት ውስጥ፣ በመተላለፊያ ቦታ ላይ ወይም በአየር መተላለፊያ የተጠጋ ቦታ ላይ ያካተተ ነው።

በቤት ውስጥ የካርቦን ሞኖክሳይድ ክምችትን በሮችንና መስኮቶችን በመክፈት ለመከላከል አይቻልም።

በተጨማሪም የካርቦን ሞኖክሳይድ ጋስ ይወጣ ዘንድ ጀነራቶሩ ከተከፈቱ መስኮቶች፣ በሮችና አየር መውጫ መራቅ አለበት።

በቤትዎ ውስጥ በባትሪ ድንጋይ የሚሰራ ለካርቦን ሞኖክሳይድ ማስጠንቀቂያ አላርም ወይም የካርቦን ሞኖክሳይድ አላርም ከባትሪ ጋር በተጨማሪ መግጠም።

ከጀነራቶሩ የካርቦን ሞኖክሳይድ ጋዝ ወደ ቤትዎ የሚገባ ከሆነ እና የጤና ችግር የሚያመጣ ከሆነ ታዲያ በአላርሙ አማካኝነት ማስጠንቀቂያ ማግኘት ይችላል። በተደጋጋሚ የባትሪ ድንጋዩ መሥራቱን ማየትና ካስፈለገ መቀየር ነው።

## በኤሌትሪክ ሞትን ማስወገድ

- ጀነራቶሩ ደረቅ ሆኖ መያዝና በዝናብ ወይም በርጥበት ሁኔታዎች ላይ አለመጠቀም።
- ከእርጥበት፣ ክፍት በሆነ ደረቅ ቦታ ላይ ጀነራቶሩን ለመከላከል፣ ማለት በምሰሶ የተደገፈ የዝናብ ልብስ።
- ጀነራቶሩን ከመንካትዎ በፊት እጅዎ እርጥብ ከሆነ ማድረቅ ይሆናል።

## ጀነራቶሩ እንደገና ነዳጅ መሙላት

- እንደገና ነዳጅን ከመሙላትዎ በፊት ጀነራቶሩን ማጥፋትና ማቀዝቀዝ ይሆናል። በሞቀ የሞተር ክፍል ላይ ፐትሮል ነዳጅ ስለሚንጠባጠብ ሊቃጠል ይችላል።
- የፐትሮል ነዳጅን ከመኖሪያ ቦታ አርቆና በተቆለፈ ጥላ ቦታ ወይም የማያሰጋ ቦታ ማስቀመጥ ነው።
- የሆነ ነዳጅ በሚቀጣጠል የኤሌትሪክ መሳሪያ አጠገብ አለማስቀመጥ (ለምሳሌ፤ በተፈጥሮ ጋዝ የውሃ ማሞቂያ ጋራጅ)።

## ከጀነራቶር ጋር የተያያዙን የኤሌትሪክ መሳሪያ ስለመጠቀም

- የኤሌትሪክ መሳሪያውን በቀጥታ ወደ ጀነራቶሩ መስካት። በአማራጭ ጠንካራ የሆነ ከቤት ውጭ የኤሌትሪክ ገመድ መጠቀም ይህም ያለው ሃይል መጠን (ዋትስ ወይም አምፕስ) ቢያንስ ከኤሌትሪክ መሳሪያው ጋር ተመጣጣኝ መሆን አለበት።
- ገመዱ ምንም ስንጥቅ ወይም ቅዳጅ አለመኖሩን ማረጋገጥና በተለይ በመሬት ላይ የሚሰካው መስኪያ ሶስት ማስገቢያ ጣቶች አሉት።
- ከግድግዳ ላይ የሚሰካ ጀነራቶር በቤት ውስጥ የኤሌትሪክ ገመድ "መልሶ መጠቀም" የተባለ አሰራር በምንም አለመሞከር ነው። ይህም በጣም አደገኛ የሆነ አሰራር ሲሆን ታዲያ በሰራተኞችና በጎረቤታሞች ተመሳሳይ የሃይል መስተላለፊያ በሚጠቀሙት ላይ የኤሌትሪክ ሞት ችግርን ሊፈጥር ይችላል። በተጨማሪም በቤቱ ውስጥ በተገጠሙ አንዳንድ የኤሌትሪክ ደህንነት መሳሪያዎችን ሊተላለፍ ይችላል።

## ለካርቦን ሞኖክሳይድ መርዝነት ስለመከላከል ምክሮች

- ቤቱን ለማሞቅ የጋዝ ውጤቶን ወይም ምድጃ አለመጠቀም።
- በቤት፣ በድንኳን ወይም ካራቫን ውስጥ የክሰል መጥበሻ፣ ፋኑስ ወይም በካምፕ ተንቀሳቃሽ ምድጃ በምንም መልኩ አለመጠቀም።
- የጀነራቶር መሳሪያ በባለሞያ ካልተገጠመና ያየር ጪስ ማውጫ ከሌለው በስተቀር በምድር ቤት፣ በጋራጅ ውስጥ ወይም በሌላ አጠገብ ሆኖ በተከፈተ በር ወይም መስኮት አጠገብ ቢሆንም እንዲሰራ አለማድረግ ነው።
- በተለይ ሃይለኛ ነፋስ ካለ ስብርባሪውን በአየር መውጫና መግቢያ ሊዘጋው ስለሚችል የቤት ውስጥ አየርና ጢስ ማውጫ መስመርን ከስብርባሪ ነጻ አድርጎ መጠበቅ ጥሩ ነው።
- መስኮት፣ በር ወይም የጢስ ማውጫ ክፍት በሆነበት ከቤት ውጭ ሞተር ተሽከርካሪ፣ ጀነራቶር፣ በአየር ግፊት ማጠቢያ ወይም በነዳጅ ሃይል ያለ ሞተርን በምንም አይነት አለመጠም።
- ከማኪና ማቆሚያ ወይም ከጋራጅ አጠገብ ተሽከርካሪ ሞተሩ እየሰራ በምንም አይነት አለመተው።
- ሊያምዎ፣ እንቅልፍ እንቅልፍ ማለት ወይም መድከም ሲጀምርዎ ገለል በማለት አዲስ አየር መውሰድ — አለመዘግየት ነው።
- በካርቦን ሞኖክሳይድ ጋዝ መጋለጥዎን ከተጠራጠሩ ወዲያውኑ ይህክምና ምክር ያስፈልግዎታል።

## ለበለጠ መረጃ

በካርቦን ሞኖክሳይድ ጋዝ መጋለጥ ምክር ለማግኘት ሐኪምዎን ማነጋገር ነው።

ስለካርቦን ሞኖክሳይድ ጋዝ አጠቃላይ መረጃ ለማግኘት በሰብአዊ አገልግሎት መምሪያ የአካባቢ ጤና ክፍልን (DHS) በልክ 1300 761 874 ማነጋገር ነው።

ስለ ጋዝና ኤሌትሪክ ያለችግር ለመጠቀም መረጃ ለማግኘት በቪክቶሪያ የ ኤሌትሪክ ድህንነት/Energysafe Victoria በስልክ (03) 9203 9700 ማነጋገር ወይም በድረገጽ www.esv.vic.gov.au ላይ ማየት።

ጋዝ ሲያንጠባጥብ ወይም ለድንገተኛ ችግር ጊዜ  በስልክ 132 771 መደወል።

የዚህን ጽሁፍ ወረቀት ተጨማሪ ቅጅዎችን ለማግኘት በአካባቢ ጤና ክፍል ድረገጽ www.health.vic.gov.au/environment/emergency_mgmnt/index.htm ላይ ማውጣት።

## መጥቀሻ ጽሁፎች


ከድንገተኛ አደጋ በኋላ የካርቦን ሞኖክሳይድን መርዛምነት ለመከላከል (2006) በሰብአዊ አገልግሎት መምሪያ፣ የበሽታ መቆጣጠሪያና መከላከያ ማእከል/CDC

ለህዝብ ጤና ጥበቃ እውነታ ወረቀት — ጀነራቶር ሲጠፋ ያለችግር ለመጠቀም (2005) በኩዊስላንድ መንግሥት፣ የኩዊስላንድ ጤና/Queensland Health, Queensland Government።